# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በውጭው ዓለም ያሳለፈችው ታሪክ እስካሁኑ ዘመን ድረስ ባጭሩ

*በእደ ማርያም እጅጉ ረታ*

## በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከሀገራችን ውጭ መስፋፋት የጀመረችው ገና ከጥንቱ ነው። ለመጀመሪያም ጊዜ በአራተኛው ክፍለ ዘመን በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ኢትዮጵያውያን ገዳማት መሥርተው እንደነበ ር በ386 (እ.አ.አ) በኢየሩሳሌም የነበረው የላቲን ቤተ ክርስቲያን አባት ቅዱስ ጀሮም ጽፎታል። በዘመን የቀደሙ ደጋጐቹ አባቶቻችን ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት በቤተ ልሔም ፣ በተጠመቀበት በዮርዳኖስ ፣ በተሰቀለበት በቀራንዮ ፣ በጎልጎታ ፣ እንዲሁም በጌቴ ሴማኒ እ መቤታችን ተቀብራ በነበረችበት፣ በጽዮን ተራራ ፣ አብርሃም ልጁን ይስሐቅን መስዋዕት ባቀረበበት ወዘተ. . . በመሳሰሉት ቦታዎች ገዳማትን መሠረቱ። ይህን በሚያደርጉበት ጊዜ የኢትዮጵያውያን ነገሥ ታት ዕርዳታ አልተለያቸውም ነበር።

ለምሳሌ ዐፄ ካሌብ መንበረ መንግሥታቸውን ትተው ወደ ምንና ወደ አባ ጴንጤሌዎን ገዳም ሲሄዱ የን ግሥና ዘውዳቸውን በቀራንዮ ባለው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይቀመጥ ዘንድ ልከዋል። በዛጔ ዘመነ መንግሥትም ንጉሥ ሐርቤ (11ኛው ክፍለ ዘመን) በገንዘብ በሁሉም በሚያስፈልጋቸው ይረዳ እንደነበርና ከሌሎች ሀገሮች ጋር በገዳሙ አማካኝነት ግንኙነቱን ይፈጽም ነበር። እንደ አውሮጳ አቆጣጠር በ1422 አካባቢ ሡልጣን ባርቢ ጌታችን የተቀበረበትን ቦታ በዘጋ ጊዜ ፤ ከዚህ አድራጎቱ ካልተቆጠበ ድርጊቱ ወደ ጦርነት እንደሚያመራና ባስቸኳይ እንዲከፈት ዐፄ ይስሐቅ አድርገዋል። በ14ኛው ክፍለ ዘመንም ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ በገንዘብም ሆነ በማንኛውም ነገር ይረዷቸው ነበር። እንዲያውም ከዘይላ ከሚገኘው ቀረጥ 100 ወቄት ወርቅ በየሁለት ዓመቱ እንዲላክላቸው አድርገዋል። ደብዳቤና መጻሕፍትን በመላክም ያበረታቱዋቸው ነበር።

በ16ኛው ክፍለ ዘመን በግራኝ አህመድ ወረራ የተነሳ በኢትዮጵያ መንግሥትና በኢየሩሳሌም በነበሩ አባ ቶች መሐከል የነበረው ግንኙነት በመቋረጡ ከፍ ያለ ችግር ላይ ወደቁ። በገንዘብም እጦት በምግብም ችግር የተነሳ ከጥቂቶቹ በስተቀር ብዙዎቹ ወደ ሌላ ሀገሮች እየተሰደዱ ሄዱ። የቁጥራቸውን ማነስና፣ አቅም እንደሌላቸው የተረዱት የግሪክና የአርመን ቤተ ክርስቲያኖች እነዚህን ታሪካዊ ቦታዎች ለመንከ ባከብ ፣ ለመጠበቅ በሚል ሰበብ በቱርክ ፍርድ ቤት ሙግት ጀምረው ግሪኮች አሸነፉ። የተሸነፉት አር መኖችም ተስፋ ሳይቆርጡ የተቀሩትን ቦታዎች በዘዴ ለመውሰድ በችግር ላይ ያሉትን አባቶች ሊረዱዋ ቸው እንደፈለጉ ሆነው ቀረቡዋቸው። በምግባቸውም በሌላም በሚያስፈልጋቸው እየረዱ በዘዴ ከእጃቸ ው ጌታችን የተቀበረበትን ዋናው ቦታ ለእነሱ ወስደው ትንሽ የመጸለያ ቦታ ተውላቸው። የሆኖ ሆኖ ግ ራኝ ድል ተደርጎ መንግሥት እየተጠናከረ ሲመጣ፣ አባቶችም ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም እየተመለ ሱ አንዳንዶቹን ቦታዎች በማስመለስ አገልግሎታቸው ቀጠሉ፤ ቁጥራቸውም እየጨመረ ሄደ።

በ1774 እ.አ.አ ኢብራሂም ጃዋርድ የሚባል ግብጻዊ በእንግድነት መጥቶ በዴር ሱልጣን ገዳም ተቀመጠ ። እሱም በእንግድነቱ ጊዜ የኢትዮጵያውያኑን ችግርና ድክመት ተገንዝቦ ፤ ከሌሎች ግብጻውያን ጋር በመተባበር ቦታውን ለመንጠቅ በተደረገው ግጭት ብዙ አባቶች እየተጎዱ ሲኖሩ ሁኔታው ከዚያ ጊዜ አንስቶ እልባት ስላላገኘ ይኸው አሁንም በየዓመቱ ተመሳሳይ ግጭት ይታያል። ይህ በእንዲህ እያለ በ ዚያን ጊዜ ዘመነ መሳፍንት የሚባለው ክፍለ ዘመን ስለነበር አሁንም አባቶቻችን እርዳታ ባለማግኘታቸ ው ችግር ላይ ወደቁ። ብዙዎችም አባቶች በ1838 እ.አ.አ አካባቢ በተነሳው የተላላፊ በሽታ አለቁ። ይ ህንንም አጋጣሚ በመጠቀም ግብጻውያኑ የኢትዮጵያውያኑ እቃዎች ተላላፊ በሽታው እንዲስፋፋ ያደር ጋሉና እናቃጥላቸው በማለት በወቅቱ በጦርነት ድል አድርጎ ኢየሩሳሌምን የያዘውን ግብጻዊው ኢብራሂ ም ፓሻን በማስፈቀድ፤ ባለቤትነታችንን የሚያረጋግጡትን ሰነዶች ሰብስበው አቃጠሏቸው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮም ግብጾቹ ንብረታችንን ወሰዱ። በ1862 ፊይን የተባለው የእንግሊዝ ቆንስል ለሰር ቦላር ግብጻው ያኑ በኢትዮጵያ ላይ ስለሚያደርሱት በደል እንዲህ በማለት ጽፏል «ለእርስዎ ላሳውቅ የምፈልገው ግብ

ጳውያኑ በአበሻ ሰዎች ላይ ይህ ነው የማይባል ግፍ እየፈጸሙ ነው፤ ወንድና ሴቶችን አለምንም ልዩነት እየደበደቧቸው ነው። ከሁሉም በላይ ግብጻውያኑ የአበሻዎቹን ቤተ ክርስቲያን ቁልፍ ሰብረዋል።

በፓሻውም አለመኖር የተነሳ እኔ ምንም እርዳታ ላደርግላቸው አልቻልኩም. . . አለመታደል ሆኖ ይህ አንዱ ሁኔታ ጭካኔ ከምንም የበለጠ ለወደፊቱ ቀጣይ ችግሮች አስተዋጽኦ ያደርጋል። ይህንንም አጋጣሚ በመጠቀም አርመኖቹና ግብጾቹም አዲስ ፍርደ ገምድል ሥራ በአበሻዎቹ ላይ እያካሄዱ ነው።» ለዚህም ነው የግብጹ ፓትርያርክ ቄርሎስ ኢትዮጵያን ሲጎበኙ በመጡበት ወቅት ዐፄ ቴዎድሮስ «. . . እናንት ሽረኞች፣ እርጉም ግብጾች። በራስ አሊ ጊዜ ከእስላሙ መሪ ጋር በመሆን በኢየሩሳሌም በሚኖሩት አባቶች ላይ ሰይጣናዊ የሆነ ምክር መከራችሁ። ገረፋችኋቸው፣ ካሉበትም አስወጣችኋቸው፣ መጻሕቶቻቸውንና ማስረጃዎቻቸውን አቃጥላችሁ ቦታችንን ቀማችሁን» በማለት የተናገሩት።

በ1867 የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ቄስ ማሌት በማስታወሻቸው ላይ «እነዚያን ምስኪን አበሻዎች በጌታችን በተቀበረበት ቤተ ክርስቲያን አደባባይ፣ መተላለፊያ ላይ መንፈሳቸው በተሰበረ ሁኔታ በጸሎት እየተማጸኑ ፊታቸውን ወደ ግድግዳው ቆመው አየሁ። ትዕግስታቸውና ፍጹም ታዛዥነታቸው ካሉበት የተሻለ እድል ሊኖራቸው በተገባ ነበር፤ ይህን ችግራቸውን በመመልከት የብሪታንያ መንግሥት ሊረዳቸው ይገባል» በማለት ዘግበዋል።

የሆኖ ሆኖ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ግን የነገሡት ነገሥታት በገንዘብ ሆነ በሐሳብ መርዳት ስለጀመሩ ሁኔታዎች እየተለወጡ መጡ። ዐፄ ቴዎድሮስ በኢየሩሳሌም ለሚገኙት አባቶች ምንም ማድረግ ባይችሉም የእንግሊዝ መንግሥት እንዲንከባከባቸውና ጉዳያቸውን እንዲያስፈጽምላቸው አድርገዋል። ይህም በዐፄ ቴዎድሮስና በእንግሊዞች መኻከል በተፈጠረው አለመግባበት የዲፕሎማቲክ ግንኙነቱ እስኪቋረጥ ድረስ ቀጥሏል። ከዐፄ ቴዎድሮስ በኋላ የነገሡት ዐፄ ዮሐንስ 4ኛ በየጊዜው በደብዳቤ በማበረታታት በገንዘብም ከመርዳት በተጨማሪ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ጎዳና ተብሎ በኋላ በተሰየመው መንገድ ላይ ቤተ ክርስቲያን (ደብረ ገነት ኪዳነ ምህረት) ይታነጽ ዘንድ ከቱርኮች ጋር ሲዋጉ የተማረከ 6 ሳጥን ወርቅ ወደ ኢየሩሳሌም ልከዋል።

ዐፄ ዮሓንስ ካረፉ በኋላ ንጉሠ ነገሥት ተብለው ዘውዱን የጫኑት ዐፄ ምኒልክ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት የሚኖሩት አባቶች እነዚያን ታሪካዊ የሆኑ ቦታዎች ለተከታዩ ትውልድ ለማስተላለፍ ሲጠብቁ የሚበሉትም ሆነ የሚለብሱት እያጡ ከአርመን ገዳም በሚሰጣቸው መቁነን ብቻ እየኖሩ ከፍ ያለ ችግር እንደደረሰባቸው ሁኔታውን በማጤን ዐፄ ምኒልክ ከባለቤታቸው ከእቴጌ ጣይቱ ጋር በመሆን ቋሚ የሆነ የገቢ ምንጭ እንዲኖራቸው ለማድረግ ቆርጠው ተነሡ። በመጀመሪያ ዐፄ ዮሐንስ አስጀምረውት የነበረውን የደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን እንዲያልቅ ገንዘብ ላኩ።

በ1895/6 እቴጌ ጣይቱ በኢየሩሳሌም ለሚኖሩት ኢትዮጵያውያን ቋሚ ገቢ እንዲኖራቸው በማሰብ እዚያው ኢየሩሳሌም ውስጥ ሕንጻ ተሠርቶ የሚከራይበት መሬት እና ተጨማሪ ሌላ ባለሁለት ፎቅ ሕንጻ በዚያው ዓመት በመግዛት አበርክተዋል። በመቀጠልም ዐፄ ምኒልክ ግንቦት14 ቀን 1905 እ.አ.አ በኢየሩሳሌም ለሚኖሩት ኢትዮጵያውያን 200,000 ማርትሬዛ ብር ሰጥተዋል። ይህ ገንዘብ በባንክ ተቀምጦ ከሚገኘው ወለድ ማኅበረሰቡ እንዲጠቀምበት አድርገዋል። ርዳታቸውም በዚህ አላበቃም ፤ በዓመቱ ሌላ ሁለት ሕንጻዎችን አሠርተው ለገዳሙ አበርክተዋል። በተጨማሪም ሌላ 100,000 ማርትሬዛ ብር ለገዳሙ ዕድሳት ለግሰዋል። በኢትዮጵያና በግብጽ መሐከል በዴር ሡልጣን የተነሳውን ችግር በዲፕሎማሲያዊ መንገድ እልባት እንዲገኝለት በማሰብ ዐፄ ምኒልክ መልክተኞችን ወደ ቊስጥንጥንያ (ቱርክ)፣ ኢየሩሳሌም፣ ካይሮና ሩሲያ ከ1890 እስከ 1907 እ.አ.አ ልከዋል። በ1905 ዐፄ ምኒልክ ደጃዝማች መሸሻ ወርቅን ስለ ዴር ሡልጣን ጉዳይ በተመለከተ እንዲነጋገሩ ወደ ቊስጥንጥንያ ላኩ። በዚያው ዓመት ኒኮላ ቼድቭሬ የተባለ የሩሲያ ዜጋ የኢትዮጵያውያን በኢየሩሳሌም ቅዱሳን ቦታዎች የባለቤትነት መብት የሚያረጋግጡ ሰነዶችን ብዙ ገንዘብ ከፍሎ ከቊስጥንጥንያ ቤተ መዘክር (አርካይቭ) ውስጥ አገኘ። እንደሚታወቀው ሁሉ ከዚያ በቀደሙት ዘመናት ግብጻውያን ተላላፊ በሽታ ገብቷል በሚል ሰበብ ያሉትን መዛግብት ሁሉ ማቃጠላቸው ይታወቃል። ይህ የተገኘው ሰነድ ከቀረበ በኋላ በቊስጥንጥንያ የሚገኘው ፍርድ ቤት አንዱ ቁልፍ ለኢትዮጵያውያን እንዲሰጥ ቢወስንም በወቅቱ ኢየሩሳሌምን ያስተዳደር የነበረ ውገዢ ለግብጾቹ ስላደላ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሳይፈጸም ቀርቷል።

በ1907 ዐፄ ምኒልክ በመታመማቸው የተነሳ የዴር ሱልጣን ጉዳይ ለጊዜው ቆመ። በወቅቱ በአዲስ አበባ የነበረው የሩሲያ ዲፕሎማት ኢትዮጵያ በኢየሩሳሌም ስለተነጠቁባት ቦታዎች የሚያሳዩትንና ባለቤትነትዋን የሚያረጋግጡትን ማስረጃዎች ለማግኘት የምታደርገውን ጥረቷን ለመንግሥቱ አስታወቀ።

የሩሲያ መንግሥትም ሁኔታውን ካጠና በኋላ የቀሩትን መዛግብቶች ከቱርክ ቤተ መዛግብት ለማግኘት የ ሚችለውን እንደሚያደርግ አረጋገጠ። የሩሲያ መንግሥትም የሚፈልጉትን ሰነዶች ከቱርክ ቤተ መዘክር( አርካይቭ) ለማግኘት አመቺ ወቅት መጠበቅ ነበረበት። በ1910 በቱርክና በጣሊያን መካካል ጦርነት ሲነ ሳ ሩሲያ አጋጣሚውን በመጠቀም ገንዘብ አሰባስበው የጦር መርከብ ገዝተው ለቱርኮች ሰጡአቸው። ይ ህም በሁለቱ ሀገሮች መሐከል የጠበቀ ግንኙነት ለመመሥረትና ወደ ቱርክ ቤተ መዘክር ገብተው ሰነዶ ችን ለመመልከት እድሉን ከፈተ። እንደተጠበቀውም ሩሲያኖች ኢትዮጵያ በኢየሩሳሌም ላሉዋት ቦታዎ ች ባለቤትነትዋን የሚያረጋግጡትን ማስረጃዎች አገኙ። በወቅቱ ሩሲያ በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን እ ንዲኖራት ትፈልግ ስለነበር ከሚመለሱት 12 ቦታዎች 2 ለሩሲያ እንዲሰጥ የሚስማሙ ከሆነ እነዚህን ማስረጃዎች ለኢትዮጵያ መንግሥት እንደሚሰጡ አስታወቁ። የኢትዮጵያ መንግሥትም በውሉ እንደሚስ ማማቃል ገብቶ ሕጋዊ ስምምነት ለመፈራራም መልእክተኞች መንገድ ጀምረው የ1ኛ ዓለም ጦርነት በ መጀመሩ መልእክተኞቹ ጉዞአቸውን አቋርጠው ተመለሱ። ከዚያም ወዲያው በመቀጠል የዛሩ ንጉሥና ቤተሰቡ በጥቅምቱ አብዮት ወቅት ተገደሉ። ከቤተሰቡ መሐከል የተረፈው ልዑል አሌክሲስ ሚካኤሎ ቪች እነዚያን ጠቃሚ መረጃዎች ይዞ ከሩሲያ ወጣ።

በ1924 ልዑል አሌክሲስ እነዚያን ጠቃሚ መረጃዎች በዓለም አቀፍ ሕግ ላይ ባለሙያ ለሆነው ለባሮን ቦሪስ ኖድል እንዲመለከታቸውና እንዲመረምራቸው ሰጠው። ባለሙያውም ከማስረጃዎቹ እንዳገኘው «ማስረጃዎቹ እንደሚያመለክቱት ኢትዮጵያውያን በቅዱሱ ቦታዎች ላሉዋቸው ገዳማትና የጸሎት ቤት ከ1834 እና 1841 በፊት ባለቤት ለመሆናቸው አለምንም ጥርጥር ይመሰክራሉ በማለት አጠቃሎታል።» በ1925 ልዑል አሌክሲስ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት እነዚህን በጣም ጠቃሚ የሆኑ ማስረጃዎች ለኢት ዮጵያ መንግሥት በስጦታ አበርክቷል።

ምንም የባለቤትነታችንን መብት የሚያረጋግጡትን ሰነዶች በእጃችን ቢገቡም ችግሩ በእንጥልጥል እያለ የሁለተኛው ዓለም ጦርነት በተነሳበት ወቅት የጣሊያን መንግሥት ኢትዮጵያን ሙሉ በሙሉ ስለተቆጣጠ ርኩ በኢየሩሳሌም የሚገኙት የኢትዮጵያ ገዳማት ይገባኛል በማለት በወቅቱ ፓለስታይንን ታስተዳደር በ ነበረችው በእንግሊዝ ፍርድ ቤት ሙግት ጀመረ። እንግሊዝ የጣሊያንን ወረራ ከደገፈችው አንጻ በመ ሆኗና ፍርድ ቤቱም ለጣሊያን ቢፈርድም ጉዳዩ ውስብስብ ስለሆነ ውሳኔው ተፈጻሚነት እንዲኖረው ለ ማድረግ ጊዜ ወሰደ። በዚህ መሀል ፋሽስት ኢጣሊያ በመሸነፏ የፍርድ ቤቱ ሙግት ተዘጋ።

በ1951 አቡነ ፊልጶስ በኢየሩሳሌም የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ሆነው ተሹመው ሄዱ። እን ደ ደረሱም ወዲያው የዴር ሱልጣንን ጉዳይ በወቅቱ ኢየሩሳሌምን ያስተዳደር በነበረው በዮርዳኖስ መ ንግሥት ፍርድ ቤት ከ10 ዓመት በላይ የወሰደ የባለቤትነት ጥያቄ ድርድር አካሄደዋል። ፍርድ ቤቱም ማስረጃዎቹን ከተመለከተና ካመዛገበ በኋላ በየካቲት 22 ቀን 1961 እ.አ.አ. የዴር ሱልጣን ገዳም ለኢት ዮጵያውያን ይገባል በማለት ፈረደ። ፍርዱንም በመቃወም የግብጽ ፓትርያርክና ፕሬዜዳንት አብደል ና ስር ለዮርዳኖስ መንግሥት ተቃውሞ አቀረቡ። የዮርዳኖስ መንግሥትም ጉዳዩ ላልተወሰነ ጊዜ እንዲቆ ይ ነገር ግን ሁሉ ነገር ከዚያ ቀደም ይሠራ እንደ ነበር ይቀጥል በማለት ዘግቶታል።

በዚህ መሀል በዩም ኪፑር ጦርነት ጊዜ እስራኤል ኢየሩሳሌምን ስትቆጣጠር ይህ ጉዳይ እንደገና ወደ እስራኤል መንግሥት ቀርቦ ጉዳዩን የሚያጣራ ኮሚቴ ቢቋቋምም ከመጨረሻ ውሳኔ ላይ መድረስ አልቻ ለም። ስለዚህም በያመቱ በፋሲካ አካባቢ ተደጋግሞ ከግብጻውያን በኩል የሚታየው ኢክርስቲያናው ባህ ርይ አሳዛኝና አባቶቻችንንም ለከፍተኛ አደጋ የተጋለጡ አድርጓቸዋል።

ገዳሙም እንዳለፉት ክፍለ ዘመናት በገንዘብ በኩል ያለው ችግሩ ተወግዶ በአሁኑ ወቅት ብዙ አባቶች የሚያገለግሉ ሲሆን በምድር እስራኤል ለሚኖሩም ብዙ ኢትዮጵያውያን ከፍ ያለ አገልግሎት ይሰጣል። በነቢዩ ሶፎንያስም እንደተነገረው «ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የሚማልዱኝ፣ የተበተኑት ልጆቼ ቁርባኔን ያመጡልኛል» ሶፎ. 3፤10 ባለው መሠረት በየዓመቱ ብዙ ኢትዮጵያውያን ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ከ በረከቱ ይሳተፋሉ፤ ቤተ ክርስቲያንም ልጆቿን በመንፈሳዊ በረከት አጥግባ ተንከባክባ ትሸኛቸዋለች። ቤ ተ ክርስቲያናችንም በኢየሩሳሌም፣ በቤተልሔም ፣ በኢያሪኮና በዮርዳኖስ አገልግሎት ትሰጣለች።

እነዚህን ታላቅ የታሪክ ቦታዎች አባቶቻችን ስንት መከራ ተቀብለው እንዳስተላለፉልን እኛም እያንዳን ዳችን የመጠበቅ፣ የመርዳት እንዲሁም ገዳማችንን የሚጠብቁልን አባቶች ላይ በደል ሲፈጸም መቆርቆ ርና በተቻለን ሁሉ ለሚገባው ክፍል አቤት ማለት ይኖርብናል። አሁንም የደጋጎቹ አባቶቻችን ጸሎት እ ና በረከት በእኛ ላይ ይኑር።

## ቤተ ክርስቲያን በሌላው የዓለም ክፍል

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በውጭው ዓለም ከቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ሌላ የተ መሠረተችው በጣም ቆይቶ ከ1600 ዓመታት በኋላ በዚህ ክፍለ ዘመን በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ወቅት በጊዜያዊነት በእንግሊዘ፣ በኬንያ፣ በሱዳን፣ በጅቡቲ ነበር። በወቅቱ ስደተኞች ወደ እነዚህ ሀገሮች ተሰደው ስለሄዱ ቤተ ክርስቲያንም መንጋዎቿን የመጠበቅ፣ የማጽናናት ኃላፊነት ስላለባት ተከትላቸው ተመሥርታለች።

በእንግሊዝ ሀገር የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን በወቅቱ በስደት ላይ ለነበሩት ለዐፄ ኃ/ሥላሴና ለቤተ ሰቦቻቸው ነበር። እሳቸውም በወቅቱ በኢየሩሳሌም ለነበሩት ለእጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ አገልጋይ ካህናትና አስፈላጊውን መገልገያ ዕቃዎች እንዲልኩላቸው በጥር 13 ቀን 1929 ዓ.ም (እ.ኢ.አ) ደብዳቤ ጻፉ። በ ድብዳቤው መሠረት 5 ካህናትን፣ ታቦተ መድኃኔዓለምንና አስፈላጊውን ንዋየ ቅድሳት አሲዘው ወደ እን ግሊዝ ሀገር ላኳቸው። ይህችም ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በባዝ ከተማ ነበር። የፋሽስት ጦር ድል ተደርጐ ነፃነት ሲመለስ በስደት የነበረው ታቦተ መድኃኔዓለም ከ4 ዓመት በኋላ በሚያዚያ 23 ቀን 1933 ዓ.ም አዲስ አበባ ገባ። ከዚያም የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም ተብሎ ከስድስት ኪሎ በ ላይ ተፈሪ መኮንን ት/ቤት ጐን ተመሠረተ።

እንዲሁም በሌሎቹ የኢትዮጵያ ጎረቤት ሀገሮች በሱዳንና፣ በኬንያ፣ በጅቡቲ በጊዜያዊነት ቤተ ክርስቲ ያን ተመሥርታ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ከነፃነት በኋላ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገር ሲመለሱ እሷም ተመልሳለች።

የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ኢትዮጵያ በበለጠ በሌላው ዓለም እንድትታወቅ ያደረጋት ሲሆን በተለይ በካ ረቢያን የሚኖሩ ዜጎች አፍሪቃ የመጀመሪያ ሀገራቸው አድረገው በማየታቸው በተለይ ኢትዮጵያን የቀደ ሙ አባቶቻችን ሀገር ናት በማለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዚያ እንድትመሠረ ትና በቅኝ ግዛትና በርቀት የተነሳ የተረሳውን እምነታቸውንና ባህላቸውን እንደገና እንዲያውቁት ጠየቁ። በጥያቄውም መሠረት በ1952 ዓ.ም (እ.ኢ.አ) የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በአቡነ አትናቴ ዎስና በአቶ አበራ ጀምበሬ በትሪኒዳድ፣ ቶቤጎ፣ ጉያና ተመሠረተ። ቤተ ክርስቲያን በእነዚህ ደሴቶች ላይ እየተስፋፋች ሳለ በአሜሪካ የሚኖሩት ተመመሳሳይ ጥያቄ በማቅረባቸው በ1959 ዓ.ም (እ.ኢ.አ) ብጹ እ አቡነ ቴዎፍሎስ ኒውዮርክ ከተማ ሄደው ከመሠረቱ በኋላ ወደ ትሪኒዳድ፣ ቶቤጎ፣ ጉያና በመሄድ ቤተ ክርስቲያንን ጎበኙ። ቤተ ክርስቲያንም ከዚያ ጀምሮ ወደ ሌሎቹ ደሴቶች እየተስፋፋች በአሜሪካ ም ሌላ ግዛቶች በሎስ ኤንጀለስ፣ ዋሽንግተን እንዲሁም ካናዳ ተመሠረተች።

በ1970 ዓ.ም (እ.ኢ.አ) ቤተ ክርስቲያን በጃማይካ በአባ ላዕከ ማርያም ማንደፍሮ (አቡነ ይስሐቅ) ተመሠ ረተች። ይህ በካረቢያን የሚካሄደው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መስፋፋት ከሀገር ርቀው በአውሮጳ በ እንግሊዝ የሚገኙት የካረቢያን ዜጎች ለእነርሱም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በለንደን እንድትመሠረት ጽኑ ፍላጎት ስለነበራቸው በጃማይካ ከሚገኙት ከአባ ላዕከ ማርያም ማንደፍሮ ጋር ግንኙነት ፈጠሩ። እ ሳቸውም ሁኔታውን ለማጥናት በግንቦት ወር 1966 ዓ.ም (እ.ኢ.አ) ወደ እንግሊዝ ሀገር መጡ። ከጋበዟቸ ው ምእመናን ጋር ተገናኝተው ብዙ ምእመናንን አስተምረውና አጥምቀው ተመለሱ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተጸጽፈው ስምምነት ላይ በመድረሳቸው በጥቅምት ወር 1967 ዓ.ም (እ.ኢ.አ) አባ አረጋዊ ወ/ገብርኤል (በኋላ አቡነ ዮሐንስ) ለአገልግሎት ተልከው መጡ። እሳቸውም የካረቢያኑን ተወላ ጆች እያስተማሩ፣ እያጠመቁ ቤተ ክርስቲያንን እያቋቋሙ ሳለ አብዮቱ ከፈነዳ በኋላ ብዙ ኢትዮጵያው ያንም ከሀገር እየተሰደዱ ወደ ተለያዩ ሀገሮች ሲወጡ ብዙዎች ወደ እንግሊዝ ሀገር መጡ። በለንደን ለካረቢያን የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን አሁን ደግሞ በስደት ያሉት ኢትዮጵያውያን ጭምር ይጠቀ ሙባት ጀመር። አገልግሎቱ እስከዚያ ድረስ በእንግሊዘኛ ስለነበር የኢትዮጵያውያኑ ቁጥር ሲጨምር በ ሀገራችን ቋንቋ ለመገልገል ኢትዮጵያውያኑ ለብቻቸው በለንደን ቤስዋተር ከ1980 ዓ.ም (እ.ኢ.አ) ጀምሮ ራሳቸውን ቻሉ። የለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም በአውሮጳ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ስትሆ ን ከዚያ ቀጥሎ በጀርመን እንዲሁም በሌሎችም የአውሮጳ ሀገሮች ቤተ ክርስቲያን ተቋቁማለች። በአ ሜሪካ በብዙ ከተሞች የተቋቋመች ሲሆን፣በአፍሪቃም በሱዳን፣ በጅቡቲ፣በኬንያ፣በዑጋንዳ፣ በደቡብ አፍሪቃ፣በአውስትራሊያና በመካከለኛው ምሥራቅም ለተከታይ ምእመናኖቿ አገልግሎት እየሰጠች ነው።

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር**